የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፩
አዲስ አበባ ጥር ፮ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

16th Year No. 11
ADDIS ABABA 14th January, 2010

ማውጫ

CONTENTS

አዋጅ ቁጥር ፮፻፷፬/፪ሺ፪ ዓ.ም

ለህብረተሰብ አቀፍ የተቀናጀ የተፈጥሮ ሀብት አስተዳደር ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ አንዲውል ከዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ...... ገጽ ፭ሺ፩፻፺፬

Proclamation No. 664 /2010

International Fund for Agricultural Development Financing Agreement for Community Based Integrated Natural Resources Management Project Ratification Proclamation Page 5194

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፷፬/፪ሺ፪

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የግብርና የልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለህብረተሰብ አቀፍ የተቀናጀ የተፈጥሮ ሀብት አስተዳደር ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፬ሚሊዮን፬፻ሺ ኤስ.ዲ.አር. /አራት ሚሊዮን አራት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር./ የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራ-ሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም ዓቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ጁን ፲፱ ቀን ፪ሺ፱ በሮም የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴ-ራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታህሣሥ ፳፯ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም ያፀደቀው ስለሆነ፤

በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀፅ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለህብረተሰብ አቀፍ የተቀናጀ የተ-ፈጥሮ ሀብት አስተዳደር ፕሮጀክት ማስፈፀ-ሚያ አንዲውል ከዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅ ደቂያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፷፬/፪ሺ፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 664/2010.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE PROJECT FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL FUND FOR AGRICALTURAL DEVELOPMENT

**WHEREAS,** a Project Financing Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Fund for Agricultural Development stipulating that the International Fund for Agricultural Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan in an amount not exceeding SDR 4,400,000 (Four million Four hundred thousand SDR) for financing Community Based Integrated Natural Resources Management Project was signed in Rome on 19th day of June 2005;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Represent - atives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the Agreement at its session held on the 5th day of January, 2010;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 sub article (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Fund for Agricultural Development Financing Agreement for Community Based Integrated Natural Resources Management Project Ratification Proclamation No.664 /2010."

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ጁን ፲፱ ቀን ፪ሺ፱ በሮም የተፈረመው ቁጥር 777-ET የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፬ሚሊዮን፬፻ሺ ኤስ.ዲ. አር. /አራት ሚሊዮን አራት መቶ ሺ ኤስ. ዲ.አር./ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር ፮ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement No. 777-ET signed in Rome on the 19th day of June 2009 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Fund for Agricultural Development is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of SDR 4,400,000 (Four million four hundred thousand SDR) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement;

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 14th day of January , 2010**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**